በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

# የከተማ ፕላን ረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ

ግንቦት 2009

አዲስ አበባ

# የከተማ ፕላን ረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ

## 1. መግቢያ

የአንድን ሀገር የከተማ ዕድገት ጤናማ በሆነ ሁኔታ ለመምራት ከአገራዊ የከተማ ልማት ፕላን አንስቶ በየተዋረዱ እስከ የገጠር የልማት ማዕከላት ድረስ ተመጋጋቢ የሆኑ ልዩ ልዩ የፕላን ዓይነቶች በማዘጋጀት ከተሞችንና የገጠር የልማት ማዕከላትን መምራት ይገባል፡፡ ለዚህም ሲባል ለፊዚካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና መልካም አስተዳደር አፈጻፀም ይረዳ ዘንድ ግልጽና አሰሪ የሆነ የህግ ማዕቀፍ፣ እቅድና የሥራ መመሪያ ሊኖር ይገባል፡፡ ማንኛውም ፕላን ሲዘጋጅ ከአገራዊና ከክልላዊ የከተማ ልማት ማዕቀፍ ጋር የተሳሰረ በማድረግ፣ ወቅቱንና ተጨባጭ ሁኔታዎችን ያገናዘበ፣ አሳታፊና ችግር ፈቺ በመሆን፣ ጠንከር ያለ የፕላን ዝግጅትና ትግበራ ክትትልና ድጋፍ አሰራር በመዘርጋት ለዘላቂ ዕድገት አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም አጠቃላይ የአገሪቱን የእድገት አቅጣጫ መሠረት ያደረገ የከተማ ፕላን ህግ በማዘጋጀት የከተሞችንና የገጠር የልማት ማዕከላትን ዕድገት በፕላን መምራት ያስፈልጋል፡፡

ይህ ረቂቅ አዋጅ በሚዘጋጅበት ጊዜ አስፈላጊውን ግብዓት ለማሰባሰብ ሲባል ከክልሎችና ከተለያዩ የከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ የከተማ አመራሮችና በከተማ ፕላን ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሙያዎች እንዲሁም ለሌሎች ባለድርሻ አካላት በተለያዩጊዚያት ረቂቅ ሰነዱን በስልጠና መልክ በማቅረብ አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ ግብአቶች ተሰባስበው ተካተውበታል፡፡

## 2. የከተማፕላን ረቂቅ አዋጅ እንዲዘጋጅ ያስፈለገበት ምክንያት

### 2.1.አዋጅ ቁጥር 574/2000 በአፈጻፀም ረገድ የታዩበትን ክፍተቶች ለማስተካከልና ተጨማሪ አሰራሮችን ማከል በማስፈለጉ

ቀደም ሲልሲ ሰራበት የነበረውና ከተሞችን በፕላን ለመምራት ታስቦ የተዘጋጀው አዋጅ ቁጥር 574/2000 በአፈጻፀም ረገድ የታዩበትን ክፍተቶች በመገምገምና ለከተሞቻችን ጤናማ ዕድገት የሚበጁ ተጨማሪ አሰራሮችን በማከል እንዲሁም ወቅቱ በፈጠረው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ሳቢያ ከተሞቻችን በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉ ከመሄዳቸውም ባሻገር በየክልሎቹ በብዛት

እያቆጠቆጡ ያሉትን የገጠር የልማት ማዕከላት በፕላን ለመምራት የሚያስች ልሁኔታን ግምት ውስጥ በማስገባት አዋጁን እንደገና መቃኘትና ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## 2.2 . የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን በሚፈለገው ደረጃ ለማሳካት

በአሁኑ ወቅት አገራችን እየተከተለችው ካለው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ አንጻር ከተሞቻችን በይዘትም ሆነ በቁጥር በፍጥነት እያደጉ በመሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ ግብርና-መር ኢኮኖሚው ወደ ኢንዱስትሪ-መር ኢኮኖሚ በሚያደርገው የሽግግር ሂደት ከተሞች ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ከተሞች የኢንዱስትሪ ልማት በማስፋፋት፣ ኢንቨስትመንትን በመሳብና የኢኮኖሚ እድገት ስበት ማዕከል በመሆን በ2017 አገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለማሰለፍ የተያዘውን አገራዊ የትርንስፎርሜሽን እቅድ ለማሳካት እንዲቻል ተጨማሪ የፕላን አሰራርና ማስፈጸሚያ ህጎች ከወቅቱ ሁኔታ አንጻር መቃኘት ስላስፈለገ የከተማ ህጉንም እንደገና ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## 2.3. አዳዲስ የፕላን ዓይነቶችን ማካተት በማስፈለጉ

በከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስትራቴጂ የተጠቀሱትን አዳዲስ የፕላን ዓይነቶች ማለትም ስትራቴጂክ ኘላን፣ መሠረታዊ ፕላን፣ ስኬች ኘላንና የከተማ ዲዛይን በረቂቅ አዋጁ ውስጥ በማካተት እውቅና መስጠት በማስፈለጉ እንዲሁምየከተሞች መሠረታዊ ካርታ ዝግጅት ሁኔታ ግልጽ በሆን አሰራር ለመምራት፤ የ30፣ 30 እና 40 የመሬት አጠቃቀም ምጣኔ መርህን ስራ ላይ ለማዋል፣ የመሰረተ ልማት መረቦች ዝረጋታ በከተማ ፕላን መሰረት እንዲሆን ለማድረግና ለመሳሰሉት ጉዳዮች ሲባል አዲስ አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

## 2.4. የህብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ባለቤትነት አጉልቶ ማሣየት በማስፈለጉ

በከተማ ፕላን ዝግጅትና አተገባበር ዙሪያ ህብረተሰቡና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የፕላን ፍላጎት ከማመንጨት አንስቶ በዝግጅት፣ በማጽደቅና በትግበራ ሂደት ወቅት በተለይም በከተማ ማስፋፊያ ምክንያት ለሚነሱ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች እንዲሁም በመልሶ ማልማት ለሚነሱ ዜጎች ኑሯቸዉ በዘላቂነት የሚቀጥልበት ሁኔታ ግምት ዉስጥ በማስገባት የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማድረግ የባለቤትነት ሚናቸው ጎልቶ እንዲታይ ማድረግ ይቻል ዘንድ በህግ ማዕቀፍ ውስጥ ማካተት በማስፈለጉ፡፡

### 2.5. የፕላን ጥሰት የሚፈጽሙትን በህግ ተጠያቂ ማድረግ በማስፈለጉ

የፕላን ዝግጅትና ትግብራን በተቀመጡ ህጋዊ አሰራሮች መሰረት በማያከናዉኑ አካላት ላይ ተመጣጣኝና አስተማሪ የሆኑ ቅጣቶችን በአዋጁ ውስጥ ማካተት የፕላን ጥሰትን መከላከል በማስፈለጉ፡፡

## 3. የከተማ ፕላን ረቂቅ አዋጅይዘት

የከተማ ፕላን ረቂቅ አዋጁ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች እንደ አዲስ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት አዋጁ በአምስት ክፍሎችና በ30 አንቀጾች የተደራጀ ሲሆን የክፍሎቹ ይዘት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. ክፍል አንድ፡- ጠቅላላ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን በውስጡም
   - አጭር ርዕስ
   - ትርጓሜ
   - የተፈፃሚነት ወሰን
   - መሰረታዊ መርሆዎች ተካቷል፡፡
2. ክፍል ሁለት፡- ስለከተሞች ወሰን፤ መሠረታዊ ካርታና የፕላን ተዋረዶች የያዘ ሲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች አካቷል፡፡
   - የከተሞች ወሰን
   - መሠረታዊ ካርታ
   - ሀገራዊ የከተማ ልማት ፕላን
   - ክልላዊ የከተማ ልማት ፕላን
   - ከተማ-ዓቀፍ ፕላንና ዝርዝር የማስፈጸሚያ ፕላኖች
   - ስኬች ፕላን
3. ክፍል ሶስት፡- ስለፕላን ዝግጅትና ትግበራ የያዘ ሲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች እንዲያካትት ተደርጓል፡፡
   - የፕላን ሀሳብ ስለማመንጨትና ስለማዘጋጀት
   - ፕላን ስለማጽደቅ
   - የፀደቁ ፕላኖችን ስለማስተዋወቅና ቅጂ ስለመስጠት
   - ፕላኖችን ስለመተግበር

- ፕላኖችን ስለመከለስና ማስተካከል

4. ክፍል አራት፡- ስለ ልዩ ልዩ አካላት ሥልጣንና ተግባር የያዘ ሲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች አካቷል፡፡
    - የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር
    - የክልል መንግሥታት ሥልጣንና ተግባር
    - የከተማ አስተዳደሮች ሥልጣንና ተግባር
    - የወረዳ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር
5. ክፍል አምስት፡- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች የያዘ ሲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች አካቷል፡፡
    - ቅጣት
    - የመተባበር ግዴታ
    - የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች
    - ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን
    - አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

በአጠቃላይ ከላይ ከመነሻ ሀሳቡ ጀምሮ እንደተገለፀው የአገራችንን የዕድገት አቅጣጫና የወቅቱን የከተሞቻችን ፈጣን ዕድገትና እንቅስቃሴ መሠረት በማድረግ፣ እንዲሁም ደግሞ ከዚህ በፊት በአሰራር ዙሪያ ይታዩ የነበሩትን ክፍተቶች ለማረም በሚያስችል መልኩ ሲሰራበት የነበረውን የከተማ ኘላን አዋጅ በአዲስ መተካት በማስፈለጉ አዲሱ አዋጅ ከላይ በተዘረዘረው ቅርጽ መሠረት ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡